# የካሊፎርኒያ ዩኒቨርሲቲ፣ ሳንፍራንሲስኮ
# የሚሞከርባቸው ሰዎች
# መብቶች ዝርዝር

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት መብቶች በጥናት ላይ እንዲገኙ የሚጠየቁ ሰዎች ሁሉ መብቶች ናቸው። እንደ አንድ የጥናት መሞከሪያ የሚከተሉት መብቶች አሉኝ፡

1) ጥናቱ ለማወቅ የሚሞክረው ነገር ምን እንደሆነ የማወቅ፣
2) ምን እንደሚደርስብኝ፣ እንዲሁም ማንኛውም ዓይነት የሕክምና ሂደት፣ መድኃኒቶች ወይም መሣሪያዎች በመደበኛ አሠራር ጥቅም ላይ ከሚውሉት የተለዩ ስለመሆናቸው የማወቅ፣
3) ተደጋጋሚ እና/ወይም አስፈላጊ ስለሆኑ ስጋቶች፣ የጎንዮሽ ጉዳቶች ወይም ለምርምር ዓላማ ሲባል ስለሚደርሱብኝ ነገሮች ምቾት ማጣቶች የማወቅ፣
4) ከመሳተፍ ልጠብቅ የምችለው ማንኛውንም ጥቅም ካለ፣ እና ይህ ከሆነ፣ ይህ ጥቅም ምን ሊሆን እንደሚችል የማወቅ፣
5) ስላሉኝ ሌሎች ምርጫዎች እና እንዴት በጥናቱ ውስጥ ከመሳተፍ የተሻሉ ወይም የከፉ ሊሆኑ እንደሚችሉ የማወቅ፣
6) በጥናቱ ላይ ለመካፈል ከመወሰን በፊትም ሆነ በጥናቱ ሂደት ወቅት ጥናቱን የተመለከተ ማንኛውም ጥያቄ የመጠየቅ ፈቃድ፣
7) ማንኛውም ዓይነት ውስብስብ የጤና ችግር ቢከሰት ምን ዓይነት ሕክምና ማግኘት እንደሚቻል የማወቅ፣
8) ፈጽሞ ላለመሳተፍ የመወሰን ወይም ጥናቱ ከተጀመረ በኋላ ተሳትፎን በተመከተ ሃሳብ የመለወጥ። ይህ ውሳኔ በጥናቱ ውስጥ ባልሳተፍ ኖሮ የማገኘውን እንክብካቤ የማግኘት መብቴን አይነካም፣
9) የተፈረመ እና ቀን የሰፈረበትን የስምምነት መስጫ ቅጽ ቅጂ የመቀበል፣
10) በጥናቱ ላይ ለመካፈል ፈቃደኛ መሆን እፈልግ እንደሆነና እንዳልሆነ ስጠየቅ ከምንም ዓይነት ጫና ነፃ መሆን።

የምርምር ጥናቱ በምግብ እና የመድኃኒት አስተዳደር (FDA) ቁጥጥር የሚደረግበት መሆን አለመሆኑን የጥናት ዶክተሬ ይነግረኛል። ይህ ጥናት በፌዴራል የምግብ፣ የመድኃኒት እና የመዋቢያ ሕግ (FD&C ሕግ) መሠረት ቁጥጥር የሚደረግበት ከሆነ፣ FDA በጥናቱ ውስጥ ያለኝን ተሳትፎ የሚመለከቱ ሁሉንም መዝገቦች ሊፈትሽ እና ሊገለብጥ እንደሚችል እገነዘባለሁ።

---

ሌሎች ጥያቄዎች ካሉዎት ተመራማሪውን ወይም የምርምሩን ረዳት መጠየቅ ይኖርብዎታል። በተጨማሪም፣ በምርምር ፕሮጀክቶች ውስጥ የተሳታፊዎችን ጥበቃ የሚመለከተውን የተቋማዊ ግምገማ ቦርድ (Institutional Review Board, IRB)ን ማነጋገር ይችላሉ። የ IRB ቢሮን ከሰኞ እስከ ዓርብ ከ 8:00 AM እስከ 5:00 PM በስልክ ቁጥር (415) 476-1814 በመደወል ወይም ለ UCSF Human Research Protection Program, Box 1288, 490 Illinois Street, Floor 6, San Francisco, CA 94143፣ ወይም በኢሜይል በ irb@ucsf.edu ላይ ማግኘት ይችላሉ። ስለ ትርጉሞች መረጃ ለማግኘት ወደ (415) 476-1814 ይደውሉ ወይም ወደ irb@ucsf.edu ኢሜይል ይላኩ።

የስምምነት ነጥቦቹ የቀረቡት በቃል ነው።

የተሣታፊ ስም

ለስምምነት የተሣታፊ ፊርማ

ወላጅ ወይም ህጋዊ ፈቃድ ያለዉ ተወካይ

የምሥክር ፊርማ

ቀን